# እንደገበቴ ውኃ መዋለል ለምን?

ህይወት ከአራዳ

‹‹ነጋድራስ›› ጋዜጣ በቅፅ 07 ቁጥር 202 በህዳር 4 ቀን 2002 ዓ.ም እትሙ ‹‹እንደኔ እንደኔ›› በሚል አምዱ ስር ‹‹የሥነ ምግባር ደንቡ ለመወነጃጀል የሚጋብዝ ነው›› በሚል ርዕስ የፐ/ር በየነ ጴጥሮስን አስተያየት ይሁን መልእክት አስነብቦናል፡፡ ሁኔታው አግራሞት ስለጫረብኝ የራሴን አስተያየት ልሰጥ ወደድኩ፡፡

ፕሮፌሠር በየነ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ በአይን የማውቃቸው ከመሆኑም በላይ በተቃዋሚ ፓርቲ ጐራ ከተሰለፉበት ጊዜ አንስቶ በተደጋጋሚ በግሉ ፕሬስና በቴሌቪዥን መስኮት እመለከታቸዋለሁ፡፡

ፕሮፌሰር በየነ በ1997 ምርጫ እንደነቅንጅት ጠርዝ የወጣ ቅጥ ያጣ የጥላቻን ፖለቲካ በአደባባይ ሲሰብኩና ሲያሰብኩ፣ ሲተገብሩና ሲያስተገብሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ስልጣን ምሰሶ ይሰቅለናል ያሉት የአመፅ መንገድ ጨቀጨቅ ውስጥ መግባቱን ሲረዱ ‹‹ቼ›› ይሉት የነበረውን ተከታያቸውን የራስህ ጉዳይ ‹‹ እንደገባህ ተወጣው›› በማለት ሰላማዊ መስለው የሃሰትና የሁከት መቀስቀሻ ካባቸውን አውልቀው ወደ ፓርላማ ጐራ ያሉ ፖለቲከኛ መሆናቸውን በሚገባ አውቃለሁ፡፡

ፕሮፌሰር በየነ በወቅቱ ሰላማዊ መስለው የቀረቡት ለሃገራቱና ለህዝቧ አሳቢ ሆነው ሳይሆን ለስልጣን ጥማቸው ማርኪያ የመረጡት መንገድ በህግ ፊት ከተጠያቂነት ሊያስመልጣቸው እንደማይችል ስለተረዱት ነበር፡፡ የእርሳቸውና የመሰሎቻቸው የተሳሳተ አካሄድ ግን ሀገርንና ህዝብን የማይገባ መስዋዕትነት አስከፍሏል፣ ህይወት እንዲጠፋና ንብረት እንዲወድም አድርጓል፡፡

ፕሮፌሰር በየነ ከ1997ቱ አካሄዳቸው ሊማሩት የሚገባው ነገር አንድ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ የፖለቲካ ብቃትን፣ ኃላፊነትና የህግ የበላይነትን ብቻ ሳይሆን የሞራል ተጠያቂነትንም ሊላበስ የሚገባው መሆኑን ነው፤ ሰው ከህግ በተጨማሪ ለህሊናውም መገዛት አለበትና፡፡ ከስህተት መማር ታላቅነት ነው፤ ነገር ግን ሁሌም ከስህተት መማር የለብንም፡፡ ተከታዮቻችሁንና ደጋፊዎቻችሁን ዳግም ስህተት ውስጥ እንዳትዘፍቁት በጥልቀት አስባችሁና አቅዳችሁ ብትንቀሳቀሱ ይመረጣል፡፡ እርስዎና የእርስዎ ፓርቲ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ሀገራችንን ሌላ ጥፋት ውስጥ ለመክተተ ያለመ ነውና፡፡

ፕሮፌሰሩ በ97ቱ ሁከትና ነውጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የነበራቸው ቢሆንም ኢ-ምንት የህግ ተጠያቂነት ሳያገኛቸው በፓርላማ ታዛ ተጠልለው አልፈዋል፡፡ በወቅቱ የህብረት አመራሮች የነበሩት እሳቸውና ዶክተር መራራ በነዛችሁት የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ተታለው የተከተሏችሁ አንዳንድ ደጋፊዎቻችሁ ብድሩን ከፍለዋል፡፡ እናንተና አሁንም በተቃዋሚ የፖለቲካው ጐራ የተሰለፉ አንዳንድ እናንተን መሰል የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ወደ ስልጣን መሰላል ያመራናል ብለው ያሰቡትን ሁሉ ከመተግበር ወደኋላ

የሚሉበት አንዳችም ነገር እንደሌለ በተግባር እየታየ ነው፡፡ እርስዎም ሆነ ዶ/ር መረራን የመሰላችሁ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች አቋማችሁን እንደምትዘወሩት መኪና መሪ በየቀኑ፣ በየስአቱም አንዳንዴም በየደቂቃው ሲለዋወጥ መመልከትም የተለመደ ክስተት ሆኗል፡፡

ለመሆኑ እናንተ ፖለቲከኛነትንና የአቋም ፅናትን እንዴት ትፈትሹትና ትመዝኑት ይሆን? እዚህ ላይ አንድ ሃሳብ መመልከት ብቻ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ሰሞኑን በፓርቲዎች መካከል ሲካሄድ በነበረው የምርጫ ስነ - ምግባር ደንብ ድርድር ላይ ‹‹ መድረክ ›› በሚል ስም የተሰባሰባችሁ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ድርድሩ ላይ እንሳተፋለን ብላችሁ ነግራችሁን ሳይውል ሳያድር ድርድሩን አቋርጣችሁ (ረግጣችሁ) መውጣታችሁን ነገራችሁን፡፡በዚያው ውሎ “እኛ መደራደር የምንፈልገው ከገዥው ፓርቲ ጋር ብቻ ነው” በሚል ድርድሩን አቋርጣችሁ መውጣታችሁን እንዳልነገራችሁን ዘግየት ብላችሁ ደግሞ “ምርጫ ቦርድ ስልጣኑን ስለተቀማ ድርድሩን እንድናቋርጥ ተገደናል አላችሁ”፡፡ በዚያው ምሽት ደግሞ “የስነ - ምግባር ደንቡ ከውጭ ሀገር የተገለበጠ ነው፤ እኛ ተማሪ እነሡ ሌክቸረር ሆነው ሊያስተምሩን ሲፈልጉ ድርድሩን ረግጠን ወጥተናል” አላችሁ፡፡ ምርጫ ቦርድ አንዴ “የገዥው ፓርቲ ቅጥረኛ ነው፤ ሌላ ጊዜ ብቃት ያንሰዋል” ወዘተ ስትሉ እንዳልከረማችሁ ስልጣኑን ያላግባብ ተቀምቷል በሚል አቋም ድርድር አቋርጣችሁ መውጣታችሁን ነግራችሁን አረፋችሁ፡፡

ወደ ፕሮፌሰር በየነ ልመለስና ‹‹ ነጋድራስ ›› ጋዜጣ ላይ ከሰጡት አስተያየት አንድ ሁለቱን እንመልከት፡፡ ‹‹ … ይህ አስተዳደር መቀየር አለበት፡፡ ይህ መሆን ካልተቻለ ደግሞ የፖለቲካ ድርጅቶች ተባብረን አንድ የብሔራዊ የአንድነት መንግስት ማቋቋም መቻል አለብን፡፡ ፖለቲካችን ወደዚያ እንዲያድግ ያስፈልጋል እኔ ብቻ አሸናፊ መሆን አለብኝ የሚለውም መወገድና መታረም አለበት›› ብለዋል፡፡

ክቡር ፕሮፌሰር መቼም የሃገራችን ህገ መንግስት ይጠፋቸዋል ብዬ አልገምትም፡፡ ህገ መንግስቱ በግልፅ እንዳስቀመጠው በሃገራችን ስልጣን ሊፈልቅ የሚችለው ከህዝብና ከህዝብ ድምፅ ብቻ ነው፡፡ እርስዎ ‹‹ይህ አስተዳደር መቀየር አለበት ›› ቢሉም በሃገራችን ስልጣን የህዝብ ነው፡፡ ህዝብ ይሆነኛል ያለውን ይመርጣል፣ በመረጠው አካል ላይ አመኔታ አጣሁ ካለ ከስልጣን ያወርዳል፡፡ ይህ ነው የዴሞክራሲ መገለጫው እንጂ ማንም የፖለቲካ ፓርቲ በፈለገ ጊዜ አስተዳደሩን የሚቀይረው አይደለም፡፡ የስልጣን ምንጭ የሆነውን የህዝብ መብት ወደ ጎን በማለት ፕ/ሩ ‹‹የፖለቲካ ድርጅቶች ተባብረን አንድ ብሔራዊ የአንድነት መንግስት ማቋቋም መቻል አለብን›› በማለት በአደባባይ መለፈፍ ግን ቀደም ሲል ቅንጅት ሲያራምደው ቆይቶ በኋላ በህግ ተጠያቂ ያደረገውን አቋም በግልፅ ያመላክታል፡፡

በቅርብ ቀን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከገዥው ፓርቲ ጋር “እንደ ኬንያና ዚምባብዌ ሥልጣን መጋራት አለብን” በማለት ዶክተር መረራ በአደባባይ የለፈፉትን፣ አይ ይህ ‹‹የመድረክ›› አቋም አይደለም የዶክተር መራራ ሊሆን ይችላል እንጂ በማለት የመድረክ አመራሮች ሲናገሩ ነበር፡፡ ነገር ግን

ሳይሰነባበቱ ፕሮፌሰሩም ሳያስቡትም ቢሆን የደገሙት ይህንኑ የስልጣን ፍላጐታቸው ማርኪያ የሆነውን አቋራጭ መንገድን መጠቀም ነው፡፡

ለፕሮፌሰሩ አንድ የምለው ነገር አለ፡፡ ፓርቲያችሁ በመጪው ምርጫ የሕዝብን ድምፅ እንደማያገኝ ቀድማችሁ ስታውቁት "የብሔራዊ አንድነት መንግሥት እንዲቋቋም እንፈልጋለን" በማለት ማላዘን ጀመራችሁ፡፡ "የብሔራዊ አንድነት መንግሥት" ሊቋቋም የሚችለው ግን የአገር ሠላም አደጋ ላይ በወደቀ ጊዜ ብቻ መሆኑ እየታወቀ ሕገ መንግስታዊ ሥርዓትና የሕግ የበላይነት በተከበረባት አገር እንዲህ ያለ በአገርና በሕዝብ ላይ መሟረት ምን ይሉት ጫወታ ይሆን? ፕሮፌሰር እርስዎና ፓርቲዎ ሊገነዘቡት የሚገባ ነገር በአገራችን ብቸኛው የሥልጣን ምንጭ የሕዝብ ድምፅ ብቻ መሆኑን ነው፡፡

ክቡር ፕሮፌሰር እንዳሉት ‹‹የብሔራዊ አንድነት መንግስት›› ለመመስረት ምርጫ መካሄድ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ህገ መንግስታችንንም እንደገና መከለስ ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም ህገ - መንግስቱ በግልፅ እንዳስቀመጠው አብላጫ ድምፅ ያገኘ ፓርቲ መንግስት ይመሠርታል እንጂ እርስዎ እንደሚያሟርቱት ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ እንዲቋቋም አይፈቅድም፡፡ይህ አካሄድም ከህግ አንፃር ለእርስዎም ሆነ ለፓርቲዎ ተጠያቂነትን ሊያመጣ እንደሚችል ልብ ሊሉት ይገባል፡፡

ሌላው ላነሳ የምፈልገው ነገር ፕሮፌሰሩ በመልእክታቸው ላይ ‹‹ይህ እንደራደርበት የሚሉት የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ብዙም ፋይዳ ያለው ነገር አይደለም›› ብለው ነግረውናል፡፡ ክቡር ፕሮፌሰር የ97ቱ አይነት የአመፅና የሁከት መንገድ እደናፈቀዎት ይቀራታል እንጂ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ሕዝብም ሆነ በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሠላምንና የሠላም መንገድ ብቻ ናፍቀዋል፡፡ ከዚህ ውጭ በአመፅና ሁከት ሥልጣን ለማግኘት የሚደረግን እንቅስቃሴ አገሪቱም ሕዝቡም ሊሸከመው የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ለእርስዎ መንገር የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ ክቡር ፕሮፌሰር የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ የእርስዎንና የመሰል ፓርቲ ደጋፊዎችን ከመስመር እንዳይወጡና ሁከትና አመፅ እንዳይቀስቅሱ ቢያግዝ እንጂ ለሰላማዊ ተወዳዳሪ ደንቃራ እንዳልሆነ ማንም ይመሰክራል፡፡ሁከትንና ነውጥን ጥላ አድርጎ ስልጣን ለመያዝ ለሚሯሯጥ ግን በርግጥም እርስዎ እንዳሉት ላይበጅና እንቅልፍ ሊነሳ ይችላል፡፡

ለህግና ሥርዓት መገዛት፣ ሀገርንና ህዝብን ከጥፋት በመታደግ የሰላም መንገድንና ሰላማዊ ትግልን መምረጥ ለማንም የሚጠቅም ቀና መንገድ ነው፡፡ መድረክ ማለትም የእርስዎ ፓርቲ በስነ - ምግባር ደንቡ ድርድር ላይ ላለመሣተፍ በተለያየ ጊዜ ሶስት ምክንያቶችን ማለትም "የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ አይነት" አቅርቧልና የቱን እንመን? የቱ ነው እውነተኛው ምክንያት? አንድ ያገሬ ከፍተኛ ፖለቲከኛ በአንድ ወቅት ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ ‹‹የምወደው ሰው ትክክልም ይሁን የተሳሳተ ሃሳብ፣ ሰው ላመነበት አቋም በፅናት ሲቆም ያስደስተኛል›› ያሉትን ልጥቀስልዎት ወደድኩ፡፡ እውነት ነው እንደገበቴ ውሃ መዋለሉ ጥሩ አይመስለኝም፡፡

የእርስዎ ፓርቲ መጀመሪያ ድርድሩን አቋርጦ ለመውጣቱ የሰጠው ምክንያት ከገዥው ፓርቲ ጋር ብቻ መደራደር አፈልጋለሁ የሚል ነበር፡፡ ይህ ካልሆነ ድርድሩን ረግጠን እንወጣለን አላችሁ በተግባር አሳዩን፤ ሰንበትበት ብለው ደግሞ ይህን የስነ - ምግባር ደንብ የምርጫ ቦርድ ሊያወጣው ሲገባ ሌላ አካል ማውጣቱ ተገቢ አይደለም፣ ምርጫ ቦርድ ስልጣኑን ተነጥቋል  የሚል ሌላ ሰንካላ ምክንያት ማሠማት ጀምራችሁ እንዳልነበር አሁን ደግሞ ይህ አልሆን ሲል የምርጫ ስነ - ምግባር ደንቡ ጠቀሜታ እንደሌለው በማጣጣል ልትነግሩን እየሞከራችሁ ነው፡፡

የምርጫ ስነ - ምግባር ደንቡን ገዥነት ለማጣጣል ፕሮፌሰሩ የተናገሩትም አስገራሚ ነው፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት - ‹‹ድርድሩ መካሄድ ያለበት መሠረታዊ ፋይዳ ባለው ጉዳይ ነው፡፡ መሠረታዊነት በሌለው ጉዳይ ላይ ተቀምጠው ሁለት ወር አጠፋን የሚሉ ሰዎች ያሳዝኑኛል፡፡›› ለመሆኑ ክቡር ፕሮፌሰር ለብጥብጥና ለነውጥ ሽምቀቆ ማበጀት ፋይዳ አይኖረው ይሆን? ዳግም ነውጥ፣ ዳግም ሁከት፣  ንብረት ማውደምስ ለሀገራችን ይመችላታል? እርስዎንም ሆነ ዶክተር መረራን የሥልጣን መሠላል ላይ የሚሰቅል እስከሆነ ድረስ ማንም ምንም ላይ ይቁም አይመለከተንም ባይ መሆናችሁን በንግግራችሁ ማመላከታችሁ ፍፁም ያልተገባ ነው፡፡ ወደዱም ጠሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለፈው ምርጫ ትልቅ ተሞክሮ አግኝቷል፡፡ በጥቂት ፖለቲከኛ ነን ባዮች ውዥንብር ተወናብዶ በአመፅ መንገድ ለመዳከር የሚፈልግ አንድም ወጣት ኢትዮጵያዊ የለም ማለት እችላለሁ፡፡ በመሆኑም የሚበጀው መንገድ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግልን መርጦ ከምርጫ ኮሮጆ በሚገኝ ካርድ ብቻ ሥልጣን ለመያዝ መንቀሳቀስና ሰላማዊ ትግሉን መቀላቀል ብቻ ነው እላለሁ፡፡ ቸር እንሰንብት!